# ***እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2018 የነበረው***


# ***የአየር ሁኔታ ግምገማ***

*ባለፉት አስር ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በበልግ አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተስፋፍቶ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በተለይም በደቡብና በመካከለኛው ኦሮሚያ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ ይበልጥ ከመጠናከሩ ጋር ተያያዞ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከባድ ዝናብ እንዲኖር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል፤ በደቡብ እና በመካከለኛው ኦሮሚያ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በ*24 *ሰዓት ዉስጥ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በዶሎ ኦዶ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በመጣሉና ቅጽበታዊ ጎርፍ በማስከተሉ በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን በተደረገው ግምገማ ለመረዳት ተችሏል። ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በዶሎ ኦዶ* 123.9፣ *በወላይታ ሶዶ* 58.1፣ *በወራቤ* 57.5 *በናዝሬት* 56.4፣ *በሀዋሳ* 52.0 *እና* 34.0፣ *በደብረዘይት* 55.8፣ *አርባምንጭ* 36.5፣ *በሳውላ* 51.5 *እና* 43.7፣ *በዝዋይ* 45.2፣ *በአየሁ* 38.9፣ *በኤቢላ* 50.0፣ *በቡርጂ* 51.7፣ 47.0 *እና* 38.2፣ *በዶሎመና* 76.5 *እና* 30.0፣ *በጊኒር* 61.1፣ *በሀገረማርያም* 81.2፣ 34.3 *እና* 30.0፣ *በምዕራብ አባያ* 30.5፣ *በወረይሉ* 30.5 *እንዲሁም በጅግጅጋ* 44.0 *በሚ.ሜትር ይገኙበታል፡፡*


*ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከ*25-169 *ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ በደቡብና በምስራቅ ትግራይ፤ ከአማራ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ምስራቅ ጎጃምና ሰሜን ሸዋና ኦሮሚያ ክልል* 3፤ *ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የከማሺ ዞን፤ ከኦሮሚያ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ፣ እንዲሁም አርሲና ባሌ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፤ ከሶማሊ የጅግጅጋና የደገሀቡር ዞኖች፤ አዲስ አባባ እንዲሁም ድሬዳዋና፣ ሐረሪ ከ*2-10 *ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፤ የመካካለኛው ትግራይ፣ ከአማራ አብዛኛው የደቡብና የሰሜን ጎንደር፣ አገዋዊ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ አብዛኛው አሶሳ፣ ጋምቤላ፣ አፋር እንዲሁም ከሶማሌ የአፍዴር፣ የጎዴ፣ የቆራሂና የዋርዴር ዞኖች ከ*5-25 *ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ*2 *ላነሱ ቀናት ያህል ነበራቸው* (*ካርታ* 1 *እና* 2)*፡፡*

*ባለፉት አስር ቀናት የነበረው ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር በደቡብና በምስራቅ ትግራይ፤ ከአማራ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ክልል* 3፤ *ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የከማሺ ዞን፤ ከኦሮሚያ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ፣ እንዲሁም አርሲና ባሌ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፤ ከሶማሊ የጅግጅጋና የደገሀቡር ዞኖች፤ ከአፋር ዞን*1፣ 3 *እና* 5፤ *አዲስ አባባ እንዲሁም ድሬዳዋና፣ ሐረሪ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው* (*ካርታ* 3) *፡፡*

ካርታ 1     ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2     እ.ኤ.አ  ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው
የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በኤፕሪል የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በልግ አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጥሩ እርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ለበልግ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ በተለይም በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ጥሩ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ለጓሮ አትክልት፣ ለዕፅዋት ልምላሜ፣ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት መሟላት፣ ለረዥም ጊዜ የመ¤ር ሰብሎች ለማሳ ዝግጅት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከባድ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ ቅጽበታዊ ጎርፍ በተወሰኑ ቦታዎች በመከሰቱ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ባሉ ሰብሎች እንዲሁም በሰው እና በንብረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4   እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 21-30 ኤፕሪል 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው አብዛኛው ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ፣ ኦሞጊቤ በጥቂት የላይኛው የባሮአኮቦ፣ የአዋሽ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች፣ የላይኛው የአፋር ደናከል እና በጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች እንዲሁም የላይኛው የገናሌዳዋ ምስራቃዊው ክፍልና የአባይ ኪስ ቦታዎች ላይ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ደግሞ ጥቂት የአባይ ደቡባዊና ምስራቃዊው ክፍል፣ የታችኛው ኦሞጊቤ፣ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ አብዛኛው ዋቢሸበሌ፣ የአዋሽ ምእራባዊው ክፍልና የምስራቅ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች፣ አብዛኛው የአፋር ደናከልና ተከዜ እንዲሁም የአባይ የመካከለኛውና የምስራቅ አጋማሽ ተፋሰሶች ናቸው$ በተቀሩት አብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል (ካርታ 5)።

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# <u>እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10/2018 የሚኖረው</u>

# <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በሜይ የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በደቡባዊው አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚህም መሰረት <u>ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ አዲስ አበባ፤ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ ፤ አርሲና ቦሌ፣ ቦረናና ጉጂ፤ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል የከማሺና የአሶሳ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ሰሜን ሸዋ እንዲሁም ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ ከአፋር ዞን 3፣4 እና 5፤</u> <u>የደቡብ የትግራይ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኦሞ፣ እንዲሁም የሰገን ህዝቦች በተጨማሪም የሶማሌ ክልል አብዛኛው ዞኖች መደበኛና ከመደበኛው በላይ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መጠናከር ጋር ተያይዞም በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊመዘገብ ይችላል። የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።</u>

# <u>እ. ኤ. አ ከሜይ 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u>

# <u>አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥለው የሜይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች በተለይም በደቡባዊ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬአቸውን ይዘው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ከላይ በትንበያው በተጠቀሱት ቦታዎች የሚገኘዉ እርጥበት በተለየዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ልዩ ልዩ የበልግና የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እና ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚገኑ የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል። በሌላ በኩል በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ለጎርፍና ለመሬት መንሸራተት መቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር በእርሻ እንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እንዲሁም የተገኘውን እርጥበት የማቆርና የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን አጠናክረው እንድቀጥሉ ይመከራል፡፡

## እ. ኤ. አ ከሜይ 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ወደ ደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍል በመስፋፋት አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የታችኛውና የመካከለኛ አዋሽና ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የኦጋደን ተፋሰሶች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃችን ይጠቁማል። በተጨማሪም በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ የከባድ ዝናብ ክስተት ሊኖር ስለሚችል በትንንሽ ወንዞች ላይ ሙላት እና በረባዳ ስፍራዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስልሚችል ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።